IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

22070015

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Monday 14 May 2007 (morning)
Lundi 14 mai 2007 (matin)
Lunes 14 de mayo de 2007 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d’orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.



© IBO 2007

**ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ (መርጠሽ) አስተያየት ስጥ(ስጭ)።**

**1. (ሀ)**

# ነፃነት እንደናፈቀ

ይጮሃል ስልኩ
ይጮሃል
በራሱ ድምፅ እስኪሳቀቅ
ደጋግሞ ይጣራል
ወይ መርዶ ሊነግር
አሊያም ብሶት ሊያሰማ
ወይ የምስራች ሊለን
የኛን ጩኸት እየቀማ
ይጮሃል ስልኩ ይጣራል
ይጠራል
የሕፃን ልቅሶ ይመስል
አረፍ እያለ ይመጣል....
በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ
በሐዘን ሙጃ ተውጦ
ረሃብ እየገረፈዉ
ከውርደት ገንዳ ዘቅጦ
ደብዛዉን እንደ እንቁራሪት
አረንቋ ውስጥ ደብቆ
ሰቆቃውን ያሰማል
በማያቋርጥ ፍርሃት
በሰቀቀን ተዘፍቆ
ቀዳማዊውን ጥሪ
ለዘላለም እየማለ

ይጮሃል ስልኩ
“የስሚ ያለህ!” እያለ
ደራሽ ውሃ ይመስል
በቅፅበት እየዋለለ
አሁንም ይጮሃል ስልኩ
የሚደርስለት ጠፍቶ
ድረሱልኝ እያለ!
ከኤዢያ ይሁን ካፍሪካ
ካውሮፓ ወይ ካሜሪካ
ያለቅሳል ስልኩ
ያፈሳል የዕንባ ዝናቡን
ይራገማል እንዲህ የፈጠረውን
የአርባ ቀን ዕጣውን.....
ወይ ደዋዩ አላቆመ
ወይ አንሺውም አላነሳ
ዕንባውን ያፈሳል ስልኩ
ድምፁ እየሰለለ
እንደ ጅማት እስኪቀጥን
እንደርሃብ እስኪከሳ
ይጮሃል!
ስንት ጥሪ ሰምተናል
ላይከፈት የተንኳኳ
ሺ ጥያቄ አንስተናል
ላይቆጠር የተለካ
ከንቱ ሆነዉ ሊቀሩ
አረፋ ኅብስተ መና
የሚሊዮን ዕንባ ፈሷል
ጅረት ሆኖ በልመና
ግና ስንት ስልክ አለ?
ነፃነት እንደናፈቀ
እንደተራበ የገረጣ
ዘመን ሙሉ እየጮኸ
የሚያነሳው ሰዉ ጠፍቶ
አቤት የሚለዉ ያጣ::

አማኑኤል መህሪ ፣ "ነጻነት እንደናፈቀ"፣ <u>ጥለት፣</u> ቼምበር ማተሚያ ቤት፣ **1996::**

— በግጥሙ ውስጥ ነጻነት እንደምን ቀርብዋል?

— ገጣሚው በአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ::

— የግጥሙን ዋና ጭብጥ ለመረዳት ያገዙህ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

— ስለግጥሙ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ምንድነው?

**1. ለ**

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው ብለው ከገፈርሳ እስከደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች፥ ተበጀ፥ ሰካራሙ ተበጀ፥ ዶሮ ነጋዴው ተበጀ፥ ነው ብለው ይነግርዋቸዋል።

የሕይወቱ ታሪክ ፍጹም ገድል ነው። ጢም ያለው ሸማግሌ ሰው ነው። የራሱን ጠጉር ውኃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም።ማለዳ አይናገርም። በጠርሙስ የከመረውን ከጠጣ በኋላ ማታ ሲራገም ወይም ሲሳደብ ፥ሲፈክር፥ ወይም ሲያቅራራ ድምጡ ከፈረንጅ ውሻ ድምፕ ይወፍራል። ቢያውቀውም ባያውቀውም ላገኘው ሁሉ ማታ ሰላምታ ይሰጣል። ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ሁሉ ጋራ ይስቃል። ቢያውቀውም ባያውቀውም የሰላምታው ዓይነት እንደወታደር ወይም እንደሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው። ከሰላምታው ጋር ድምፕ ትሰማላችሁ። ካፉ ከሚወጣው ግን አንድ ቃል መለየት አትችሉም።

ቡን በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር የሰካራም ተረት የተጫወተው ሰው ሁሉ የተናገረ በተበጀ ላይ ነው። መልኩን አይተውት ያላወቁ ባልቴቶች እንኳ ከፍንጃል ቡኑን ፉት እያሉ የሌላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ ይላክኩት ነበር። ይህ እውነት ነበር።በጠባዩ ከተባለበት የባሰ ሰካራም ይሁን ወይም የተሻለ ከጉለሌ ባሕር ዛፍ ውስጥ ወጥቶ አንድ አዲስ እንግዳ ሰው ሆኖ ለአዲስ አበባ ታይትዋል።

ከድሮው የእንጦጦ ጉምሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው። በዚያው በቤቱ በዚያው በጉለሌ በሰፈሩ ኖረ።

እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሰራው እርሱ ነው። ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል።

ተበጀን ኩራት ተሰማው። ቆይቶ ደግሞ ዓይኖቹ እንባ አዘሉ። በጉንጩም የእንባ ዘለላ ወረደው። በግራ እጁ መዳፍ ከጉንጩ የተንከባለለውን እንባ ጨፈለቀው። ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱ ለራሱ ጎጆ ስላለው ነው። ሊነገር በማይቻል ደስታ ልቡ ተለውስዋል።

ዝናም ያባረራቸው ከቤቱ ጥግ ሊያጠልሉ ይችላሉ። ቤት የእግዚአብሄር ነውና ወዥብ እንዳያገኛቸው ከቤት ውስጥ ዝናሙ እስኪያባራ ይቆያሉ። ተበጀን "ቤትህን ይባርክ" ሊሉት ነው።

እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ "ይህ የማን ቤት ነው? ብሎ ሲጠየቅ የተበጀ ሊባል ነው" አለ።

ቀጥሎ ደግሞ "ተበጀ የትኛው ነው ሲባል ዶሮ ነጋዴው ሊባል ነው" አለ።

"ዶሮ ነጋዴው የትኛው ነው ሲባል ያ የጉለሌው ሰካራም ሊባል ነው። አወይ! እኔ ተበጀ፥ ተበላሸቻለሁ" አለና ደነገጠ። ከዚህ በኋላ ስለቤቱ ክብር እንኳ መጠጥ መተው ይገባኛል አለ።

መጠጥ ለመተው ያሰበበት የመጀመሪያ ጊዜው ይህ ነው። ሰካራምነት ጉዳት መሆኑ ተሰምቶት እንደሆን ይናገር ስለ ቤት ክብር ማለቱ ግን ወደ ዳር

ይቆይ:: ስለ ቤት ክብር ምን ያውቃል? ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ሰካራሙ ተበጀ አይደለምን?

ሰካራሙ ተበጀ የሰራውን የገዛ ቤቱን ከፍቶ ገባና ኩራዙን አስቀምጦ ክብሪቱን ለመጫር ሲያወጣ በሐሳብ ተሰቅዞ እንደዚህ አሰበ:: መምረጥ አለብኝ:: ከዚህ ቤት ያለው መጠጥ ሁሉ አንድ ሳይቀር እየወጣ ይፍሰስ፤ ከዚህ በኋላ ክብሪቱም ኩራዙም በቤት ይደር፤ በአዲሱም ቤት ብርሃን ይዙርበት:: አለዚያም በአዲሱ ቤት መጠጥ ይዙርበት! ኩራዙና ክብሪቱ ከቤት ይውጣና ይፍሰስ:: ሊደረግ የሚገባ ከሁለቱ አንዱ ነው እንጂ÷ በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳት በአንድነት ይህቺ ውሸት አለና ሳቀ::

ከሁለቱ አንዱን ለማድረግ ሳይቆርጥ መብራቱን አቃጠለና ተቀመጠ:: እንደገና ደግሞ እንደዚህ አሰበ:: አያድርገውና ዛሬ ሰክሬ ይህ ቤት ቢቃጠልብኝ አመዱን አይቶ በሰካራሙ ተበጀ ላይ ለመሳቅ ድፍን ጉለሌ ነገ ከዚህ ነው የሚቆም! ጉለሌ ምን ባለኝ? ወሬ ከማቡካት በቀር ጉለሌ ምን ሥራ አለው? ለአዲስ አበባም የስድስት ወር መሳቂያ በሆንኩ ነበር:: መንገድ አላፊዎችም ነገ በዚህ ሲያልፉ አመዱን አይተው ይህ የተቃጠለው ቤት የማን ነበረ ሲሉ የተበጀ ሊባል ነው:: በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳት ባንድነት ይህች ውሸት!

ወደ ውጭ እንደ እርም ወርውሮት የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ ሁሉ በጨለማው ዳብሶ አንድ በአንድ ለቃቀማቸው:: አንዱን ግን ቀና አደረገና ከአፍንጫው አስጠግቶ አሸተተው:: በጠርሙሱ ቅርፅ የመጠጡን ዓይነት አወቀው:: ዊስኪ ነበርና ስለዚህ ነው ሰው እንዳይሰማ ቀስ ብሎ የሳቀ:: የጠርሙሱን ግማሽ ከጠጣ በኋላ ግን ባፉ ቡሽ ቢወትፉበት ለሳቁ መጠን የለውም::

" ጉለሌ ተኝቷልና ከዚሁ ከባሕርዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ብጠጣ የሚታዘበኝ የለም" አለና አሰበ:: እውነቱን ነው:: ጉለሌስ ተኝቶ ነበር ነገር ግን አሁን እርሱ ጠጥቶ የሰከረ እንደሆነ ጉለሌን ሊቀሰቅሰው ነው እርሱ ከጠጣ በጉለሌ ውስጥ ማን ይተኛል::

ጠርሙሱን ከከፈተው በኋላ ብርጭቆ ያስፈልገው እንደነበረ ትዝ አለው:: ሶስት የሚሆን ደህና ጉንጭ ጠርሙሱን ከአፉ አስጠግቶ ጨለጠ:: ከዚያ በኋላ የሚጠጣበት ብርጭቆ ሊያመጣ አሰበ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ በሶስት ጉንጭ ምን ያህል ጠርሙሱን እንዳጎደለው ለማወቅ ጠርሙሱን ቀና አድርጎ በጨረቃዋ ተመለከተ:: "ግማሹን ያህል ሰርጉጀዋለሁ አለና በሳቅ ፈነዳ:: "ለዚችስ ብርጭቆ ማምጣት አያሻም" እያለ ጠርሙሱን አምቦጫቦጨው:: በቀኝ ክንዱ መሬቱን ተረክዞ የቀረውን ጅው አድርጎ ወደ ውስጥ ወረወረው:: ባዶውን ጠርሙስ ደግሞ በጁ እየጠነቆለ "አንተን ደግሞ ለአንድ ዶሮ ለውጬ ሞያ አስይዝሃለሁ የዊስኪ ቅርፍቱም ዋጋ አለው አይጣልም" አለ::

ተመስገን ገብሬ፣ «የጉለሌው ሰካራም»፣ <u>ልቦለድ አዋጅ እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች</u>፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ **1995**::

— በልቦለዱ ጉለሌና ነዋሪዎቹ እንደምን ቀረቡ?

— ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምን ይመስልሀል?

— በልብወለዱ ደራሲው በአንባቢው አመለከከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ::

— የአጭር ልቦለዱ መቼት ዋናውን ገፀባህሪ በማሳየት ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ ግለፅ::